# ህዳር 29–በድህነትን ላይ እንድንዘምት ያደረገን ቀን

**በላይ ሰይፉ 12-8-14**

ሀገራችንና መላው ህዝባችን ዛሬ ለተጎናጸፍናቸው የሠላም፣ ፈጣን ልማትና የዴሞክራሲ ድሎች መሰረት ለሆነው የኢፌዴሪ ህገ -መንግስት እውን መሆን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ረጅም ጊዜን የወሰደና ከፍተኛ መስዋዕትነትን የጠየቀ ትግል አካሂደዋል፡፡

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች መኖሪያ ብትሆንም፤ እነዚህ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ለዘመናት በአፈናና በጭቆና ሥርዓት ቀንበር ስር ወድቀው ሲማቅቁ ቆይተዋል፡፡ ለዚህም ደግሞ ያለፈውን የደርግ ሥርዓት ብቻ ማስታወሱ ከበቂ በላይ ማስረጃ ነው፡፡

ይህ ሥርዓት የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የእኩልነትና የነጻነት ጥያቄዎች ምላሽ ሊሰጥ ባልቻለው የፊውዳላዊ ሥርዓት ላይ የተነሳው ህዝባዊ ተቃውሞና አመጽ በፈጠረለት አጋጣሚ ያቆጠቆጠና የህዝቦችን የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤትነት በኃይል ነጥቆ በመዳፉ ማስገባት የቻለ እንደነበር ይታወሳል፡፡

የደርግ ሥርዓት ከመነሻው የህዝቦችን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ፍላጎት ያለው ኃይል መስሎ ብቅ ቢልም አጀንዳው ግን በአቋራጭ ስልጣን ለመያዝ መሆኑ በገሃድ ተስተውሏል፡፡ በመሆኑም የህዝቦችን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ አልቻለም፡፡

ይልቁንም በአፄው ሥርዓት ላይ በርትቶ የነበረውንና ደርግም ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ የቀጠለውን ህዝባዊ ተቃውሞ ለማዳፈን የኃይል ርምጃን እንደብቸኛ አማራጭ አድርጎ ተጠቅሞበታል፡፡ በዚህም እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ንጹሐን ዜጎች ያለፍርድ በመጨፍጨፍ ታሪክ ምንጊዜም የማይረሳው ወንጀል ፈጽሟል፡፡

በወቅቱ የደርግ መንግስት በዜጎች ላይ የሚወስደው ጭካኔ የተሞላበት ርምጃ ቢያይልም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ተቃውሞአቸውን ከማሰማት ብሎም ትግል ከማካሄድ የገታቸው አልነበረም፡፡ የፀረ - ደርግ ትግሉ የሚያሳየን እውነታም ይህንኑ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በደርግ ላይ በማመጽ ባካሄዱት የትጥቅ ትግል እጅግ ረጅምና ውስብስብ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ አልፈዋል፡፡ አያሌ መስዋዕትነትም ከፍለዋል፡፡ በዚህም ሂደት ውስጥ አልፈው የደርግ ሥርዓት ዳግም ላይመለስ ሥርዓተ - ቀብሩን የፈጸመበት ታሪካዊ ድል ለመጎናጸፍ በቅተዋል - በግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም፡፡

ህዝባዊ ድሉ በአንድ በኩል አምባገነናዊው የደርግ ሥርዓት ሙሉ ለሙሉ እንዲወገድ ያስገደደ ሲሆን፤ በሌላም በኩል ደግሞ በፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የምትመራ አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት መሰረት የተጣለበት ነው፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ያለገደብ የተከበረበትን ህገ -መንግስት በራሳቸው ፍላጎትና ይሁንታ ለማጽደቅ ችለዋል - ህዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም፡፡ በየዓመቱ ህዳር 29 ቀንን በታላቅ ድምቀት እያከበርን ያለነው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀንም ይህንኑ መነሻ ያደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የቃል ኪዳን ማሰሪያ ሰነድ የሆነው የኢፌዴሪ ህገ -መንግስት ጸድቆ በስራ ላይ ከዋለ ወዲህ ሀገራችን ትክክለኛ የዕድገት አቅጣጫ ይዛ በአዲስ የታሪክ ምዕራፍ ላይ በድል ለመረማመድ በቅታለች፡፡ የብሔሮችና ብሔረሰቦች እስር ቤት እስከመባል ደርሳ የነበረችው ሀገራችን፤ የህዝቦቿ መብት የተረጋገጠባት፣ የዕድገትና ልማት ብሩህ ተስፋን የሰነቀች፣ የእኩልነትና የፍትህ አምባ ለመሆን ችላለች፡፡

በመሆኑም የአፈና አገዛዝ፣ የግፍ ቀንበር ተጭኖት የኋላቀርነትና የበታችነት ተምሳሌት ተደርጎ ይታይ የነበረው የብሔር ብሔረሰቦቿ ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ የህዝቦቿ መኩሪያና መከበሪያ፣ የሀገራችን መድመቂያ ጌጥና የመልካም ገጽታዋ መገለጫ ወደመሆን ተሸጋግሯል፡፡

የተለያየ እምነትና የአኗኗር ዘይቤን የሚከተሉ የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በመግባባትና በመረዳዳት መንፈስ አብሮ በመኖር በዓለም የሚታወቁበት የመቻቻል ባህልም ከመቼውም በላቀ ሁኔታ በመዳበር ላይ ይገኛል፡፡

እነዚህ ታሪካዊ፣ ባህላዊና መንፈሳዊ የጋራ እሴቶቻችን ለሀገራችን ተጨማሪ ክብርና ሞገስ ከማላበስ አልፎ ለፈጣን ልማት ስራዎቻችን የበኩሉን ድርሻ ማበርከት ወደሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

ከምንም በላይ ደግሞ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ከሀገራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወት ተገለለውና ተረስተው በባይተዋርነት ለመኖር የተገደዱበት አድሎአዊና ፍትህ አልባ ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ተቀይሮ ዜጎች በማንኛውም ሀገራዊ ጉዳይ ውስጥ እኩል ተሳታፊ የመሆን ዕድል አግኝተዋል፡፡

ይህንንም በተጨባጭ ስራ ላይ በማዋል የሀገራችንና የህዝባችን የማደግና የመበልጸግ ተስፋን በእጅጉ ለማለምለም ችለዋል፡፡ መላው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በመብቶቻቸው እየተገለገሉና ዘላቂ ጥቅሞቻቸውን እያስከበሩ በፈጣን ልማትና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አቅጣጫ ላይ የተያያዙት ፈጣን የዕድገት ጉዞም የህዳር 29 ድል ተጨባጭ ፍሬ ነው፡፡

በሀገራችን እውን የሆነው ፌዴራላዊ የመንግስት ሥርዓት ለሀገራችንና ለህዝባችን አንድነት፣ ሠላምና ዕድገት መጠናከር ወሳኝ አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው፡፡ የዚህ አዲስ ሥርዓት ግንባታ ሂደት በተጨባጭ ተፈትኖ ፍቱንነቱ የተረጋገጠ ነው፡፡ የተገነባው ፌዴራላዊ ሥርዓት በሀገራችን ላይ አንዣቦ የነበረውን የመበታተን አደጋ ያስወገደና በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ ለተመሰረተ ከብረት የጠነከረ የህዝቦች አንድነት ዘላቂ ዋስትናን አስገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ረጅሙንና አስቸጋሪውን የትግል ምዕራፍ በድል አድራጊነት በቋጩ ማግስት በጋራ ተወያይተውና አምነው ህዳር 29 ቀን ያጸደቁት ህገ - መንግስት የዘመናት ጥያቄዎቻቸውን ሙሉ ለሙሉ የመለሰ ከመሆኑም ባሻገር፣ በቀጣይ ለሚያካሂዷቸው የጋራ አጀንዳዎች ዘላቂነትና ውጤታማነት ዋስትና የሰጠ ነው፡፡

በመሆኑም የመላው ህዝባችንን ጥያቄዎች የፈታውና ለዘላቂ ሠላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ዋስትና የሰጠው የኢፌዴሪ ህገ - መንግስት የፀደቀበት ዕለት በታላቅ ድምቀትና በልዩ ሁኔታ በየዓመቱ እየተከበረ ይገኛል፡፡

ይህ በመላው ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በታላቅ ድምቀት የሚከበረው ህዳር 29 ቀን በህዝባችን ዘንድ በተመሳሳይ ሁኔታ ተከብሯል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው የሆነው ህዝባችን ከህገ - መንግስቱ ጋር በብዙ መልኩ እጅግ የጠበቀ ቁርኝት ያለው በመሆኑ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የህገ - መንግስቱ ባለቤቶች ናቸው፡፡ ህዝቡ ህገ - መንግስቱን ያቋቋመ፣ የመንግስትን አወቃቀር የነደፈ ነው። ይህም በህገ - መንግስቱ በግልጽ ሰፍሯል፡፡ እንደሚታወሰው ያለፉት ሥርዓቶች የራሳቸው ህገ-መንግስት  የነበሯቸው ቢሆንም፤ ህዝባዊ መሰረት ግን አልነበራቸውም፡፡

ይህ የሆነው ባለፉት ሥርዓቶች በሀገራችን ህገ-መንግሥት የማይታወቅ በመሆኑ አልነበረም፡፡ እስከ ደርግ ውድቀት ድረስ በሀገራችን ሦስት የተጻፉ ህገ-መንግሥቶች እንደነበሩ ይታወሳል፡፡ ይሁን እንጂ በኃይለሥላሴ የአገዛዝ ዘመን የነበሩት ሁለት ህገ-መንግሥቶችም ሆኑ የደርግ ህገ-መንግሥት  የየስርዓቶቹን አምባገነኖች ሥልጣን ማስጠበቂያ ብቻ ናቸው፡፡ ዋነኛ ዓላማቸው የገዢዎችን ሥልጣን ማራዘምና ሥርዓታቸውን ዘለዓለማዊ ማድረግም ነበሩ፡፡

ያለፉት ሥርዓቶች ህዝባዊ አለመሆን በህገ-መንግሥታቸው ካሰፈሯቸው እውነታዎች በግልጽ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በህገ-መንግሥቶቹ ላይ ለህዝብ የሚጠቅሙ መሠረታዊ ጉዳዮች ካለመስፈራቸውም ባሻገር፤ የሰፈሩትም ቢሆን ለይስሙላ ካልሆነ በስተቀር ተፈጻሚ የሆኑ አልነበሩም፡፡

በመሆኑም ህዝቡ ገዢዎች የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ህገ-መንግስቱን እንደ መጠቀሚያ ከመጠቀም ባለፈ ተጨባጭ ተልዕኮው ምን እንደሆነ የሚያውቀው ጉዳይ አልነበረም፡፡ አወቃቀሩም ቢሆን፤ የብሔር፣ ብሔረሰቦችን ተዋጽኦ እኩል ያሳተፈ አልነበረም፡፡

ይህ ደግሞ ሠራዊቱ የህዝብና የሀገር ሉዓላዊነትን የሚያስከብር ሳይሆን፤ የሥርዓቱን ዕድሜ ለማራዘም መጠቀሚያ እንዲሆንና፣ የጥቂት ብሔር ተወላጆች ብቻ በተቋሙ ውስጥ ሚና እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡  በተጨማሪም  ዜጎች አምነውበት በፍቃዳቸው የሚሳተፉበት ሳይሆን  እየታፈኑ የሚወረወሩበት እስር ቤትም ነበር፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ህዝባችን ህገ - መንግስቱንና ህገ - መንግስታዊ ሥርዓቱ ከማንኛውም የወስጥም ይሁን የውጭ ፀረ ሰላም ሃይሎች በጽናት እንዲጠበቅላት ይሻል ፡፡ በመሰረቱ ህገ - መንግስቱ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች እንደመሆኑ፤ ህገ- መንግስቱን በማንኛውም አደጋ የመጠበቁ ኃላፊነትም የሁሉም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ነው፡፡

ይህ እውነታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ዜጋ በተደራጀ መልኩ ህገ -መንግስቱንና የሥርዓቱን ደህንነት መጠበቅ የዕለት ተዕለት ስራውና አደጋ ሊያንዣብብ ከቻለም ግንባር ቀደም ተሰላፊ የመሆን ኃላፊነት አለበት፡፡ ምክንያቱም የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ውጤት እያመጣ መምጣቱና፣ በአሁኑም ወቅትም በአጥጋቢ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ወደ ላቀ ደረጃ እየተሸጋገረ በመሆኑ ነው፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ህዝባችን የህገ - መንግስቱ ጠባቂ ብቻ ሳይሆን ተጠቃሚም መሆኑ ነው፡፡ ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደተሞከረው የኢፌዴሪ ህገ - መንግስት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የዘመናት ጥያቄን የመለሰና ለዘላቂ ሠላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ዋስትና የሰጠ ነው፡፡

ህገ - መንግስቱ ጸድቆ በስራ ላይ ከዋለ ጀምሮ ሀገራችንና ህዝቦቿ በተለያዩ መስኮች እጅግ ውጤታማ  ተግባር አከናውነዋል፡፡ እነዚህን ውጤቶች አቅቦ ከመንዝና ለአዳዲስ ድሎች ከመብቃት አኳያም በአሁኑ ወቅት መንግስትና መላው ህዝባችን በላቀ ቁርጠኝነት እየተረባረቡ ይገኛሉ፡፡ በዚህም የሀገራችን የድህነትና ኋላቀርነት ገጽታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተለውጧል፤ ሂደቱም እጅግ በተጋጋለ ሁኔታ ቀጥሏል፡፡

በሁሉም ዘርፎች የምናስመዘግበው ዕድገት ህዝባችንን በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ የህዝባችን ተጠቃሚነት ደግሞ የሀገራችንን ዕድገት የሚያፋጥን መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ሃቅ ነው፡፡

በአጠቃላይ ህዳር 29 ጸድቆ በሥራ የዋለው የኢፌዴሪ ህገ- መንግስት የኢትዮጵያን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ያለፈውን መጥፎ ታሪክ የሻረ ከመሆኑም በላይ፤ መጻዒ ዕድላቸውን ብሩህ ያደረገ ነው፡፡ ህገ - መንግስቱ በሀገራችን ታሪክ በጋራ መግባባት ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ እንዲፈጠርም አድርጓል፡፡ እንደሚታወቀው ከድህረ-ደርግ ውድቀት በኋላም የተረጋጋች እና ህዝቦቿም አንድ የጋራ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ስርዓት መስርተው እርስ በርሳቸው እየተከባበሩ በፈጠሩት ፈጣን ልማት ተቋዳሽ

የሚሆኑበትን ሀገር ለመገንባት እጅግ የመረረ ትግልን ጠይቋል፡፡ ታዲያ ይህን ሃቅ የማይቀበሉ ፅንፈኞች ትናንትም ነበሩ፣ዛሬም አሉ። ነገም መኖራቸው አይቀርም።

እርግጥ በፌዴራላዊ ሥርዓቱ ሀገራችን የተቀዳጀቻቸውን ድሎች በርካታ ቢሆኑም የቀድሞውን ስርዓት የሚናፍቁ ሃይሎች ዛሬም የብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዕለት በመጣ ቁጥር በቁጭት የማይወረውሩት የአሉባልታ ድንጋይ የለም። 1983 ዓ.ም አምባገነኑ የደርግ ሥርዓት ቢደመሰስም ለሌላ ትግል የሚጋብዙ ፈታኝ የአስተሳሰብ ተግዳሮቶች መፈጠራቸው አልቀረም፡፡ ተራማጅ የሆኑ፣ ፌዴራሊዝም ወሳኝ ለዘመናት ደም አፍሳሽ የሆነውን የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ለመፍታት ፍቱን መድኃኒት መሆኑን ያመኑ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የመኖራቸው ያህል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ሁለት ጽንፍ ጫፍ ላይ የወጡ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ ወገኖች ነበሩ።

አንደኛው በወቅቱ አስራ ሰባት የታጠቁ የብሔር ድርጅቶች ነበሩ፡፡ እነዚህ ድርጅቶች የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታን ባላገናዘበ መልኩ የችግሮች መፍትሄ መገንጣጠል ነው ብለው ያምኑ የነበሩ እና ለዚህም እንታገላለን የሚሉ ኃይሎች እንደነበሩ ያለፈው ድርሳናቸው ያወሳል፡፡ ሁለተኛው አዲሱን የሀገሪቱ መፍትሔ እና ፍቱን መድኃኒት የሆነውን የፌዴራሊዝም ሥርዓት ግንባታ እንደ መበታተን አደጋ በመመልከት ባረጀ እና ባፈጀ የአንድነት ስም የብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን እኩልነትና ዴሞክራሲያዊ መብት ብሎም መፈቃቀድን “በእኛ እናውቅልሃለን” የፖለቲካ እሽክርክሪት በማጦዝ ሀገሪቱን ወደማያባራ ቀውስ ውስጥ ለመክተት አልመው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ነበሩ፡፡

ታዲያ በወቅቱ እነዚህን ተግዳሮቶች በሰከነ ብስለት በመፍታት ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊት ሀገርን ለመመስረት ከፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ጋር ከባድ ትግል ማካሄድ ግድ ብሎ እንደ ነበርና ውጤቱም በተራማጅ ሃይሎች አሸናፊነት እልባት እንደተሰጠው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በኋላም ቢሆን ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ አልነበረም። ሀገሪቱ ለመግለጽ በሚያስቸግር መልኩ ከባድ ፈተናዎች እንደገና ከፊት ለፊቷ ተደቀነባት፡፡ ከእነዚህ ፈተናዎች የላቀ ስፍራ የያዘው እና የሀገሪቱ ዋነኛ ጠላት የሆነው “ድህነትን” የመዋጋት ዘመቻ ነው፡፡ ይህ ጠላት ዓይኑን አፍጥጦ የመጣ ጋሬጣ ሆኖባታል፡፡ ታዲያ ይህ የጋራ ጠላት የሚደመሰሰው በመንግስትና በህዝብ የተባበረ ክንድ በመሆኑ፤ ችግሩን ለመቅረፍ በቅድሚያ መንግስት የመሪነት ሚናውን በመወጣት ህዝቡን በአስተሳሰብ ደረጃ

በድህነት ላይ ድል እንዲቀዳጅ የማድረግ ኃላፊነን በሚገባ ለመውጣት ነበር ቆርጦ ወደ ትግበራ ለመግባት የተዘጋጀው፡፡

በወቅቱ ‘ድህነትን የመታገል ታላቅ ጉዞ እንዴት ሊከናወን ይችላል?፣ ይህንን የጋራ ጠላት ተዋግቶ ለማሸነፍ መሰረታዊ የሚባሉ ቁልፍ ጉዳዮችስ ምንድናቸው? ወዘተ’ የሚሉ ዋና ዋና ተግባራትን መለየት በእጅጉ ወሳኝ ነበር፡፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ግን በቅድሚያ የሀገሪቱ የበላይ ህግ የሆነው ህገ - መንግስት ማጽደቅ ግድ አለ፡፡ምንም እንኳን የሀገሪቱ የበላይ ህግ የሆነውን ህገ - መንግስት ለማጽደቅ መንግስት መድረኩን ክፍት ቢያደርገውም ፤ አንዳንድ የቀድሞ ስርዓት ናፋቂዎች ሁኔታውን በቀላሉ ሊቀበሉት አልቻሉም፡፡ ይሁንና ስልጣን ከህዝብ የሚመነጭ እንደሆነ በወቅቱ የነበረው የሽግግር መንግስት ለእነዚህ ወገኖች ማስተማሩን አላቋረጠም፡፡

እናም ስልጣን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንደሆነም በተደጋጋሚ በህዝቡ ዘንድ የማስረጽ ስራን አከናወነ፡፡ ይህን እያደረገ ባለበት ወቅት ግን ሀገሪቱ ህገ - መንግስት ሊኖራት አይገባም፣ ፌዴራላዊ ሥርዓት የምትገነባ ሀገር በምንም መልኩ ተጠቃሚ ልትሆን አትችልም የሚሉ ተቃራኒ አመለካከቶች ዋነኛ ፈተናዎች ሆነው ብቅ ብለዋል፡፡

እነዚህን ፈተናዎች ዴሞክራሲያዊ የሆነ ምላሽ እየተሰጣቸው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በገዛ ፈቃዳቸው አምነው እና ተስማምተው ህዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም የኢፌዴሪ ህገ - መንግስት አጸደቁ፡፡ ይህ ህገ - መንግስትም የቃል ኪዳናቸው ሰነድ በመሆን የኢትጵያ ህዝቦችን የዘመናት ጥያቄዎች የመለሰ እንደሆነም ያረጋገጡበት ነው፡፡ ጥቂቶቹን ተግዳሮቶች ይህን ያህል ከተመለከትን ዘንዳ ድሎቹን ደግሞ እንዲህ እንቃኛቸዋለን።

ከዚህ በኋላ ሀገርን አዋርዶ፣ ህዝብን እያሸማቀቀ ለተመፅዋችነት የዳረገን ብሎም ለዘመናት እንደ ክት ዕቃ በዚህች ሀገር ተጎልቶ ከኖረውና ድህነት ከተሰኘው ጠላት ጋር ግልጽ ውጊያ ተከፈተ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከድህነት በላይ ጠላት እንደሌላቸውም አወቁ፡፡ ይህን ለመዋጋትም የሀገራችን ህዘቦች ከሊቅ እስከ ደቂቅ በመንግስት ውጤታማ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እየተመሩ በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ዕድገት ማስመዝገብ ጀመሩ። ከድህነት አዙሪት ወደ ዕድገት እሽክርክሪት ጉዞ ይሏል እንዲህም አይደል?...

ታዲያ ህገ -መንግስቱ ጸደቆ በሀገሪቱ የፌዴራል ሥርዓት ዕውን ከሆነ በኋላ በህገ - መንግስቱ የተቀመጡት መሰረታዊ የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ጉዳዮች በሚገባ ምላሽ አግኝተዋል፡፡ ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር፣ የሚፈልጉትን ሃይማኖት በሰላማዊ መንገድ የማራመድ፣ በቋንቋቸው የመናገር እና የመጻፍ፣ ባህላቸውን እና እሴቶቻቸውን በነጻነት የመግለፅ መብቶቻቸን ህገ - መንግስቱ በማያሻማ መልኩ አረጋግጠላቸዋል፡፡ እርግጥም የዘመናት የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግልም ይህ ነበር፡፡

ሆኖም 'የፌዴራሊዝም ሥርዓት በኢትዮጵያ ተግባራዊ ከሆነ ሀገሪቱ ወደ አይሆኑ አዘቅት ውስጥ ትገባለች፣ የመበታተን አደጋ ይገጥማታል፣ ህዝቦቿ በየጎራው ተከፋፍለው እርስ በርሳቸው ይበላላሉ ወዘተርፈ' በማለት በወቅቱ በሀገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ የመገናኛ ብዙሃን የፖለቲካ ተንታኝ ሟርተኞች በተደጋጋሚ ፌዴራላዊ ስርዓታችን የማይጠቅመን አስመስለው ማራገባቸው አይዘነጋም፡፡

እርግጥ እነዚህ የመገናኛ ብዙሃንና ሟርተኞች በሀገሪቱ የተዘረጋው ፌዴራላዊ ሥርዓት ህዝቦቻችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ዘንግተውት አልነበረም— የቀድሞው ሥርዓት ናፋቂ ከሆኑት ጽንፈኛ ኃይሎች ጋር በመሰለፍ ማቀንቀኑን መርጠውት እንጂ፡፡ ዳሩ ግን እነርሱ የፈለጉትን ቢሉም መንግስትና ህዝብ በውዥንብራቸው ሳይዘናጉ ብዝሃነታቸውን ውበታቸው በማድረግ አንድነታቸውን አጠናክረው፣ ለጋራ ዕድገት መረባረቡን ነው የመረጡት፡፡

ይህን ሃቅም ዶክተር ሀሺም ቶውፊቅ በ1999 ዓ.ም "ስለ ኢ.ፌዴሪ ህገ - መንግስት አንዳንድ ማብራሪያዎች" በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ላሪያ ዳይመንድ የተባለ የውጭ ፀሐፊን ጠቅሰው እንደገለፁት፣ "ፌዴራሊዝም በማህበራዊ ምንነት ምክንያት የሚፈጠር ልዩነቶችን ለማቻቻል (አብሮ ለማራመድ) እና በማህበራዊ ምንነት ወይም በሌላ የማንነት ልዩነቶችን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን ለማስተንፈስ አግባብነት ያለው የፖለቲካ መሣሪያ ነው" ብለዋል። ይህ አብሮነትም የጋራ ኢኮኖሚያቸውን ለማሳደግ ሥርዓቱ የጎላ ሚና እንደሚጫወትም አብራርተዋል፡፡

አዎ! ይህን ዕውነታ የተገነዘበው መንግስትም ህገ - መንግስቱን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በገዛ ፈቃዳቸው ተስማምተው እና ተማምነው እንዲያጸድቁት የተጫወተው ሚና በእጅጉ የላቀ ነው፡፡ ይህችን ሀገር ከአምባገነኑ የደርግ ሥርዓት አገዛዝ ያላቀቀው ኢህአዴግ መራሹ የህዝብ ትግል፣ ስልጣን በህዝብ እና በህዝብ ብቻ የሚረጋገጥ

እንደሆነም የሚያምን በመሆኑ፤ በዚህ የሀገሪቱ የበላይ ህግ ህዝቦች የትግላቸው ባለቤት እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ ታላቁ መሪያችን በህይወት እያሉ ስለ የፌዴራሊዝም ሥርዓት አስመልክተው ያሉን መጥቀስ ያስፈልጋል። ታላቁ መሪያችን "ህገ -መንግስቱ የህዝቦቻችን የዘመናት ትግል ውጤት ነው፤ ይህን የህዝቦቻችንን የዘመናት ትግል ግምት ውስጥ በማስገባት ነው ህገ - መንግስቱ የተረቀቀው፡፡ የኢትዮጵያ ባህል ማለት የኢትዮጵያ ህዝቦች ባህሎች ተደምረው የሚፈጥሩት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋ ማለት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በሙሉ ተደምረው የሚፈጥሩት ጉዳይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት የህዝቦች ታሪክ ተደምሮ የሚፈጥረው ነገር ነው፡፡ ይህ ታሪክም በልዩነት የሚስተናገደው በፌዴራሊዝም ሥርዓት ነው" ብለው ነበር፡፡ እናም ለሀገሪቱ ብቸኛው አማራጭ የፌዴራል ሥርዓት መከተል እንደሆነም አስምረውበታል፡፡

እርግጥ ይህን የብልሁን መሪያችንን አባባል በተጨባጭ አይተነዋል፡፡ ከእርሳቸው ህልፈተ - ህይወት በኋላም ቢሆን ስርዓቱ ፈሩን ሳይስት ቀጥሏል። ምንም እንኳን ህልፈታቸው በኋላ አንዳንድ ፅንፈኞች 'ሀገሪቱ ባልተረጋጋ ውስጣዊ የፖለቲካ ችግር ትናጋለች፣ ህዝቦቿ እርስ በርሳቸው ይባላሉ ወዘተ' የሚሉ እሳቤዎችን አንዳንድ ጽንፈኛ ተቃዋሚ ኃይሎች የዕብደት ትንታኔ እየሰጡ ቢዋትቱም ይህን የሴራ አቋማቸውን ማንም እንዳልተጋራው በግልጽ ታይቷል፡፡ ምክንያቱም የፌዴራል ሥርዓቱ እነርሱ የሚሉትን አይነት በድንቡሽት የተገነባ ቤት ሳይሆን፤ በህዝቦች ፍቃድ ተረጋግጦ በጠንካራ መሰረት ላይ የተገነባ በመሆኑ ነው። እናም ሥርዓቱን ሲመለከቱበት የነበረው መነጽር የተሳሳተ ዕውነታውን የማያሳያቸው መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል፡፡

እነዚህ ጽንፈኞች የታላቁ መሪያችን ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ድንገተኛ የዜና ዕረፍት ተከትሎ ያልቀባጠሩት የወሬ ዓይነት አልነበረም፡፡ የእነርሱ የወሬ ማራገቢያ የሆኑት ሚዲያዎችን በመጠቀምም፤ 'ኢትዮጵያ ከድህረ መለስ በኋላ የተረጋጋ መንግስት አይኖራትም' የሚል ትንቢት መሳይ ቅጥፈትን ማስታወስ ይቻላል፡፡ እርግጥ እነዚህ ጽንፈኛ ኃይሎች በዜሮ ድምር የፖለቲካ ስሌት የሚመሩ በመሆናቸው ይጠቅመናል ብለው ካሰቡ ምንም ነገር ከማለት ወደ ኋላ የሚሉ አይደሉም፡፡ አሁን ከድህረ - መለስ በኋላ እነርሱ የተመኟት ኢትዮጵያ 'አለች ወይ?' ብለው እንኳን የማይጠይቁ የጨለማ ታንኳ ቀዛፊዎች ናቸው።

በክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ደንገተኛ ሞት ያልደነገጠ ኢትዮጵያዊ እና የኢትዮጵያ ወዳጅ ህዝብ አልነበረም፡፡ ህዝቡ ለመሪው የነበረውን ጥልቅ ፍቅር በይፋ አስከሬናቸው ከውጭ ሀገር በመጣ ጊዜ የወቅቱ ዝናብ እና ብርድ ሳይበግረው ከቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ጀምሮ ቤተ- መንግስት ድረስ አጅቧል፡፡ ጥልቅ ሀዘኑንም ለሁለት ሳምንት ያህል ከአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን፣ በራሱ ፍቃድ ከክልሎችና ከውጭ ሀገር በመሰባሰብ ሃዘኑን ገልጿል፡፡ ጽንፈኞቹ ግን ይህን አይተው ሲያበቁ መለስን የሚተኩ እልፍ አዕላፍ መለሶች እንዳልፈጠሩ ሁሉ ሀገሪቱ አበቃላት ሲሉ ቢሳለቁም ህዝቡ ግን ጆሮውን ሊያውሳቸው አልቻለም ፡፡

እርግጥ ከዚህ በፊት በታሪክ ልዩነታችን ውበታችን ሆኖ አያውቅም፡፡ በታሪካችን ልዩነታችን የብዝሃነታችን መገለጫ ሳይሆን በህብረ - ብሔራዊነታችን ተሸማቅቀን በአሃዳዊ ሥርዓት እንድንማቅቅ ተደርገናል፡፡ ስለዚህ ከታሪካችን ተነስተን ምላሽ ስንሰጥበት ልዩነታችን የአንድነታችን መገለጫ ሆኖ ሲያበቃ፣ ይህ ያልተዋጠላቸው የቀድሞው ስርዓት ቅሪት ኃይሎች በቃላት ስንጠቃ ተግባር መሰማራታቸው የሚገርም አይሆንም፡፡

የያኔዋ ኢትዮጵያ ዜጎቿ ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ተገፎ ያለ አንዳች የልማት ተጠቃሚነት የዘለቁ ለመሆናቸው የታሪካችን ጠባሳ አሻራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የሀገራችን ስም በእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት የችግር እና የረሃብ መገለጫ ሆኖ ሰፍሮ ነበር፡፡ የትላንቱ የተከማቸ የሀገሪቱ ችግር በአሁኑ ትውልድ ትከሻ ላይ ወድቆ ድርብ ድርብርብ ሃላፊነቱን በመወጣት ላይ መሆኑን መገንዘብ ያሻል ፡፡

በጥቅሉ የኢትዮጵያ ህዝቦች ዛሬ የፌዴራል ሥርዓቱ በፈጠረላቸው ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም በሀገሪቱ ታይቶ የማይታወቅ የልማት ዕድገት ማስመዝገባቸው አዲሱ ትውልድ በፌዴራላዊ ስርዓቱ ያስገኘው ትሩፋት ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በሀገሪቱ እየተከናወኑ ያሉ የአዲሱን ትውልድ በጎ ጅምሮች ጭቃ መቀባት ተገቢ አይመስለኝም፡፡ አዲሱ ትውልድ የሥርዓቱ አካል እንዳልሆነ፣ ያለፉት ክንዋኔዎች እርሱን እንደማይመለከቱ አድርጎ በቃላት ጨዋታ ሃቅን ሸምጥጦ መካድ አመክንዮ አልባ ጭፍን ሙግት መሆኑን አስረግጨ ልገልፅ እወዳለሁ። ታዲያ የአቶ ሰለሞን ፅሑፍ "ውሾቹ ይጮሃሉ ግመሎቹ ግን ጉዞአቸውን ቀጥለዋል" የሚለው ዓይነት ብሂል የሚያስታውሰኝ መሆኑን ሳልገልፅ አላልፍም፡፡ ያም ሆነ ይህ ይህን ታሪክዊ ድል የተቀዳጀንበትን ዕለት በልዩ ድምቀት እናከብረዋለን፡፡ የዘንድሮውን የህዳር 29 ቀን ስናከብርም በዓሉን ከማክበር በዘለለ፣ ለዚህ ህገ - መንግስት

እውን መሆን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባካሄዱት መራር ትግል ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ እንደነበራቸው እናስታውሳለን። ህገ -መንግስቱ በሥራ ላይ ከዋለ ጊዜ ጀምሮም በውስጡ የሰፈሩ ጉዳዮች ያለ መሸራረፍ ተግባራዊ እንዲሆኑና የሀገራችን ህዳሴ ጉዞ ከግቡ እንዲደርስ ግንባር ቀደም ሚና የነበራቸው የታላቁ መሪያችንን ራዕይ ለማሳካት በተሰማራንበት የስራ መስኮች ሁሉ ዳግም ቃል መግባት ይኖርብናል። አንገታችንን ባስደፋው ድህነት ላይ ዘመቻ እንድንከፍትበት ያደረገንን ይህን ቀን ስናስብ ህዳሴያችን ቅርብ እንደሚሆን በማሰብ ጭምር መሆን አለበት።